**<u>የቀድሞው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስትር እና የሕወሓትና የኢሕአዴግ አመራር አባል የነበሩት አቶ ስዬ አብርሃ ከስድስት ዓመታት እስር ከተፈቱ በኂላ ከጥቂት አጋጣሚዎች በቀር ድምጻቸው ሳይሰማ ቆይቷል፡፡ አቶ ስዬ በቅርቡ ወደአሜሪካ አቅንተው በዚያ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር ባደረጉት ውይይት የሰነዘሩዋቸው ሐሳቦች ነበሩ፡፡ በእነዚህና ከአቶ ስዬ የግል አመለካከቶች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ከዳኝነት መኮንን እና ከአሉላ ጥላሁን ጋር ካደረጉት ሰፊ ቃለ ምልልስ የሚከተለው ይገኝበታል፡፡</u>**

<u>አዲስ ነገር</u>፡- የአሜሪካ ጉዞዎ እንዴት ነበር?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- የአሜሪካ ጉዞ በሚመለከት እንደምታውቁት እኔ የኢሕአዴግ አመራር አባል ነበርኩ፡፡ በድርጅቱ ውስጥ ልዩነቱ ከተፈጠረ በኂላ ግን የኢሕአዴግ አባል አይደለሁም፡፡ ከእስር ቤት ከተፈታኹ በኂላም ቢሆን የማንም ፓርቲ አባል አልነበርኩም፤ አይደለሁም፡፡ ወደ አሜሪካ የሄድኩት በግሌ፣ በቤተሰብ ወጪ የቤተሰብ እንግዳ ኾኜ ነው፡፡

በአሜሪካ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ስብሰባ ነው ያደረግኹት፡፡ የብሔር ብሔረሰብ ማንነት ሳይለይ፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ሳይለይ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ተገኝተውበታል፡፡ የሁሉም ፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊዎች፣ የገዥው ፓርቲ ደጋፊዎችም ጭምር ተገኝተውበታል፡፡ ከማንም ፓርቲ ወገን ያልኾኑ ነገር ግን *‹‹የዚህን ሰውዬ ሐሳብ ብናዳምጠው አይከፋም››* ብለው የመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያን ተገኝተውበታል፡፡ ሰዉ እንደሚታሰበው ቁጣ ጥላቻ የሌለው መሆኑ ታይቷል፡፡ አንዳንዶች ኢሕአዴግን ለማውገዝ፣ለመርገም የሄድኩ ነው የመሰላቸው፡፡ እኔ በዚህ ዓይነቱ ነገር ውስጥ ገብቼ መንቦጫረቅ አልፈልግም፡፡ በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ላይ አትኩሬ ወደፊት መቀጠል እንጂ እነርሱ ወደሄዱበት ቁልቁለት መሄድ አልፈልግም፡፡ ሦስት ስብሰባዎች ነበር የተካሄዱት፡፡ አንዱ በዋሽንግተን ዲሲ፣ ሁለተኛው በዴንቨር ሦስተኛው በሲያትል፡፡ እንግዲህ በእንደዚህ ዓይነት ሰፋፊ መድረኮች ኢትዮጵያውያንን ለማነጋገር ዕድል ያገኘሁት አሜሪካን አገር ነው፡፡ እዚህ አገር እንዲያ ዓይነት ዕድል አላገኘሁም፡፡

<u>አዲስ ነገር፡-</u> እዚህ አገር እርስዎ ስብሰባ እንዲጠሩ ሕጉ አይፈቅድልኝም እያሉን ነው?

<u>አቶ ስዬ፡-</u> ሕጉ አይከለክልም፡፡ ነገር ግን ጣጣ ሊመጣብህ ይችላል፡፡ ኢሕአዴግ'ኮ ተቸግሮ ያለው ራሱ አምንበታለሁ የሚለውን ሕገ መንግሥት በማክበር እና ባለማክበር

መካከል ነው። ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ፣መደራጀት፣ሐሳብን በነጻነት መግለጽ ሕገ መንግሥታዊ መብት ነው። በተጨባጭ ግን እኔ ለምሳሌ ስብሰባ ልጥራ ብል ማን ነህ፤ ፈቃድ አለኽ ወይ ተብዬ እጠየቃለሁ። ካሳወቅኹኝ በኋላ ፈቃድ እንደሚያስፈልገኝ ግን በሕጉ አልተቀመጠም። ችግርም ቢፈጠር ተጠያቂ ነህ ትባላለህ።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- በአሜሪካ ቆይታዎ ከኮንግረስና ከሴኔት አባላት ጋር ተገናኝተዋል ሲባል ሰምተናል። እውነት ከሆነ በምን ጉዳዮች ላይ ተወያያችሁ?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- ከአሜሪካ በርካታ ሴኔተሮች እና ከኮንግረስ አባላት ጋር ተገናኝቻለሁ። እነርሱ ከራሳቸው ብሔራዊ የደኅንነት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በአካባቢያችን የጸጥታ ሁኔታ ላይ ይጨነቃሉ። በዚህ ጭብጥ ላይ ውይይት አድርገናል። አጋጣሚ ኾኖ የኬንያ ምርጫ ውዝግብ የተከሠተበት ወቅት ነበር። ይህም ኮሮጆ መገልበጥ የአካባቢውን ጸጥታ ምን ያህል እንደሚያደፈርስ በግልጽ ያሳያል። መንግሥትን መገልበጥ ለዓለም ኅብረተሰብ ስርቆት፣ ወንጀል፣ ሕገ ወጥ እርምጃ ነው። ለጸጥታ እና ለመረጋጋት ጠንቅ ነው በሚለው ላይ ብዙው ወገን ይስማማል። ኮሮጆ መገልበጥም መንግሥትን የመገልበጥ አንዱ ገጽታ ነው። በሥልጣን ላይ የሌሉ ሥልጣን ለመያዝ መንግሥት ይገለብጣሉ። በሥልጣን ላይ ያሉ ደግሞ ሥልጣን ላለመልቀቅ ኮሮጆ ይገለብጣሉ። ኮሮጆ መገልበጥም ትልቅ የጸጥታ ማናጋት ይፈጥራል። ይህን መሰል ችግር ሲከሠት ሃይ አለማለት ወደዳችሁም ጠላችሁም ውሎ አድሮ የራሳችሁን ደኅንነት እና ጸጥታ ይነካባችኋል ተባብለናል። ሽብርተኝነትን ማስወገድ የሚቻለው የብሔራዊ መግባባት መንግሥት ሲኖር ነው። አሜሪካ ለራሷ ጸጥታ እና ብሔራዊ ጥቅም ስትል ብሔራዊ መግባባትን ልትደግፈው ይገባታል። በኢትዮጵያም የፖለቲካ ጨዋታ ሜዳውን መፍጠር ሁሉንም ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ተወያይተናል።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- እስኪ ወደ አሜሪካው ንግግርዎ ይዘት እንግባ፤

<u>አቶ ስዬ</u>፡- ንግግሩን ያደረግኹት በአሜሪካን አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ነው። መልእክቱ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በአምስት ዋና ዋና ነጥቦች ሊከፈል ይችላል። **አንደኛ፡-** እኛ ኢትዮጵያውያን ኅብረ ብሔር አገር ነን። ይህ እውነታ እንዳለ ኾኖ ግን የብሔር ብሔረሰቦች ስብስብ አይደለንም፤ አንድ አገር ነን። ስለኾነም ለልዩነታችን ዕውቅና እና አክብሮት መስጠት ተገቢ ኾኖ ግን ደግሞ የጋራ ዕሴታችን ለኾነው ኢትዮጵያዊነት የጋራ የኾነ አክብሮት እና እንክብካቤ ልንሰጠው ይገባል። ይህን ማዳከም ኢትዮጵያዊነትን ማዳከም ነው፤ ለአጭር ጊዜ ፖለቲካዊ ጥቅም ተብሎ በልዩነቶች ላይ

ማተኮር፣ ልዩነቶችን ማድመቅ ትክክለኛ አይደለም የሚል ጭብጥ ያለው ነው የመጀመሪያው መልእክት፡፡

**ሁለተኛ መልእክት** የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ፖለቲካ ከስድሳዎቹ እና ሰባዎቹ ግራ ዘመሙ የመደብ ትግል ፖለቲካ አሁንም ድረስ አልተላቀቀም የሚል ነው፡፡ የመናቆር፣ የመሰነጣጠቅ፣ የጥል ፖለቲካ ነው፤ ‹‹የእኛ ወይም የእነርሱ›› ዓይነት የዜሮ ድምር ፖለቲካ ነው፡፡ የመራገም፣ልዩነቶችን የማድመቅ እንጂ የመከባበር፣ የመቀባበል፣ የመቀራረብ ፖለቲካ የለም፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያን ፈርጀ ብዙ ችግሮች ለመፍታት እነዚህን የፖለቲካ ዘይቤዎችን መቀየር አለብን፡፡ ጎምሳ፣ ሰባ የተቃዋሚ ፖለቲካ ባለበት አገር ቅጥ እና ዘላቂነት ያለው ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡

ሦስተኛው መልእክት፡- ልሂቃኑ በፖለቲካ አቋሞች በተለያየን ቁጥር ይህ መለያየት ወደ ኅብረተሰቡ እየተዛመተ ለዘመናት የቆየውን በጎ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እያበላሸው ነው፡፡ በተለይም አሁን ይህ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት መበላሸት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ አገር እና ሕዝብ በሌለበት ሁኔታ ስለ ዴሞክራሲ፣ ነጻነት እና ልማት ማሰብ አይቻልም፡፡ ሕዝባችንን እያጣላን፣ እያናቆርን፣ ሆድ እና ጀርባ እያደረግን እርባና ያለው ፖለቲካ መሥራት አንችልም፡፡ በማንኛውም ምክንያት በፖለቲካ ገበያ ልንለያይ እንችላለን፤ነገር ግን ሕዝብን የሚያራርቅ እና ሆድ እና ጀርባ የሚያደርግ መኾን የለበትም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ነጥቡ ከዚህ ጣጣ ፖለቲከኞች እጃችሁን አንጹ፤ እጃችሁን አንሡ፤ እጃችንን እናንሣ የሚል ነው፡፡

አራተኛው መልእክት የአገራችን ፖለቲካ መግባባት፣መቻቻል እያጣ የፖለቲካ ችግራችን እየተወሳሰበ ነው ያለው፡፡ ይህ የፖለቲካ ችግራችን መወሳሰብ ደግሞ የጸጥታ ችግርም እየኾነ ነው፡፡ ይህ የውስጣችን የፖለቲካ ችግር አያያዝ እና እያስከተለው ያለው የጸጥታ ችግር ኢትዮጵያ ካለችበት የአካባቢ የጸጥታ ችግር ጋር እየተቆራኘ አገራችንን አደጋ ውስጥ እያስገባ ነው፡፡

ገዥው ፓርቲ ይህን ነገር በትክክል እያነበበው ስለመሆኑ እጠራጠራለሁ፡፡ ዝምታ መረጋጋት ማለት አይደለም፡፡ ሰላም ማለት አይደለም፡፡ በእርግጥም ረጭ ማለት በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ አደጋ የሚያደርስ ነገር ነው፡፡ በሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል ተስፋ የመቁረጥ፣ወደ ኅቡዕ ሥራ መግባት፣ ወደ ዐመፅ፣ ወደ ትጥቅ ትግል አራማጅነት የማድላት፣ለእነርሱ ድጋፍን የማጠናከር አዝማሚያ ሊፈጥር ይችላል፡፡

**አምስተኛው መልእክት**፦ ችግራችንን በጋራ በመወያየት ነው መፍታት ያለብን የሚል ነው። ለዚህ ደግሞ አመቺ ፖለቲካዊ ሁኔታ (political space) መፍጠር፣መወያየት፣ መግባባት፣ መቻቻል፣ ሁሉንም ወገን ሊያሰባስብ የሚችል አገራዊ ማዕቀፍ ማየት፣ የምክክር መድረክ መፍጠር ያስፈልጋል የሚል ነው። ገዥው ፓርቲ ይህን ፖለቲካዊ ሁኔታ (political space) ቢፈጥር ራሱን ይጠቅመዋል። ለኢትዮጵያም ይጠቅማል።ይህ እንደ ተጠበቀ ኾኖ የአገር ጉዳይ፣ የብሔራዊ መግባባት ጉዳይ ለአንድ መንግሥት፣ ለአንድ ፓርቲ በመያዣነት የሚተው ጉዳይ አይደለም። አጠር ባለ መልኩ ያደረግኋቸው ስብሰባዎች ዋና መልእክታቸው እነዚህ ነበሩ።

<u>**አዲስ ነገር**</u>፦ *በንግግርዎ ያነሱዋቸው አብዛኞቹ ችግሮች አሁን የመጡ ሳይሆኑ እርስዎ አመራር ላይ በነበሩ ጊዜ የተፈጠሩ ናቸው። ምናልባት አሁን ብሶባቸው ይሆናል። እና አቶ ስዬ አሁን መካሪ በሆኑበት እና በአመራርነት በተሳተፉበት ሚና መካከል መስመሩ የት ነው? መጀመሪያ አቶ ስዬ እንዴት ነው መካሪ የሆኑት?*

<u>**አቶ ስዬ**</u>፦ የት ጋር ነው መስመሩ ለሚለው የትም ይሁን። ግን እኔ አንድ ነገር በታየኝ ወቅት አቅርቤዋለሁ። ስዬ ያቀረበው ጉዳይ የኢትዮጵያ አንገብጋቢ አጀንዳ ነው፤ስዬ መጨመሩ በጎ ነው ከሚባል በቀር *‹‹ለምን ስዬ ተጨመረ?››* ብሎ ጥያቄ ማንሣቱ ጥቅም ያለው መስሎ አይታየኝም። የማንኛውም ሰው ነገር መታየት ያለበት ይህ ጉዳይ እውነት እና አግባብነት ያለው አገራዊ ጉዳይ ነወይ ከሚል መሆን አለበት። በዋና አገራዊ ጉዳዮች ላይ መነጋገር ስንጀምር ቀልባችን ይሰበሰባል። አቅማችን ይሰበሰባል። <u>***እኔ የኢሕአዴግ አመራር አባል የነበርኩ ሰው ነኝ። የህወሓት መሥራች ነኝ። ስለሆነም በዚህ ድርጅት ውስጥ በሐላፊነት በነበርኩ ጊዜ ድርጅቱ ለሠራቸው በጎ ሥራዎች ሐላፊነት እንደምወስድ ሁሉ ድርጅቱ ላጠፋቸውም ጥፋቶችም ሐላፊነት እወስዳለሁ ብያለሁ።***</u> ሰው ከልምድ፣ ከትምህርት፣ ከዕድሜ ብዙ ይማራል። እኔ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ከልጅነቴ ጀምሮ ቆይቻለሁ። ብዙ ውጣ ውረዶችን አይቻለሁ። ብዙ የተማርኩት ነገር አለ። ከዚህ ትምህርት እና ከራሴ ግንዛቤ የምይዛቸው አቋሞች አሉ። ከኻያ እና ሠላሳ ዓመት በፊት እነዚህን አቋሞች ባልይዛቸው ሊያስገርም አይገባም።

<u>**አዲስ ነገር**</u>፦ *እንደሚያውቁት ኢትዮጵያ ውስጥ የመጣ መንግሥት ኹሉ ደርግም ጭምር ‹‹አዲስ ኢትዮጵያዊነት እፈጥራለሁ›› ይላሉ። ኢሕአዴግም ሥልጣን እንደ ያዘ እርስዎም ባሉበት ‹‹አዲስ ኢትዮጵያዊነት እፈጥራለሁ›› ይል ነበር። ኢትዮጵያዊነት*

ሲሉ የትኛውን ኢትዮጵያዊነት ማለትዎ ነው? ‹‹አዲሱን ኢትዮያዊነት›› ነው ወይስ የጥንት የሚባለውን?

__አቶ ስዬ__ - ይሄ የማይረባ ጥያቄ ነው፡፡ ፕሬሚሶች (ያልተገለጹ መነሻዎች) አሉት፡፡

__አዲስ ነገር-__ አዎን መነሻዎች አሉት፡፡ እርስዎ የሚስማዎትን ይንገሩኝ

__አቶ ስዬ__፡- መቼም እኔ የፈጠርኩት ኢትዮጵያዊነት የለም፡፡ ኢትዮጵያዊነት እኔ ከወላጆቼ፣ ከታሪክ የወረስኩት፣ሲያያዝ የመጣ ማንነት ነው፡፡ እርሱን ማበልጸግ፣ ማዳበር እንዳለብን አያለሁ፡፡ ከዚህም ጋር ደግሞ ከዘመን ጋር መሄድ፣ዴሞክራሲን፣ መልካም አስተዳደርን ለማጠናከር፣በፍትሕ ለመበልጸግ ለብሔር ብሔረሰብ ጥያቄዎች ዕውቅና እና አክብሮት በመስጠት፣ ዘመኑን የተገነዘበ ነገር እየጨመርን ብናዳብረው እላለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊነት አንድ ሰው፣ አንድ ትውልድ የሚፈጥረው ነገር አይደለም፡፡ከታሪክ እየተወራረሰ የሚመጣ ነገር ነው፡፡ በ1983 ዓ.ም የተፈጠረ ኢትዮጵያዊነት የለም፡፡ እኔ የፈጠርኩትም ኢትዮጵያዊነት የለም፤የወረስኩት እንጂ፡፡

__አዲስ ነገር__፡- *‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል››* ብለዋል፡፡ ይሄ ትልቅ መከራከሪያ (ክሌም) ነው፡፡ ይህን ለማለት ያስቻልዎት ምን ምልክቶች አይተዋል?

__አቶ ስዬ__፡- እኔ ይህን የምለው ከምርጫ 97 በኋላ ባየሁት ስሜት ነው፡፡ ፓርቲዎች ተፎካክረዋል፤ ተወዳድረዋል ግን እንደዚያም ኾኖ ነጻ ውይይት፣ ነጻ ፉክክር ተብሎ መጨረሻው በደም መታጠቡ የሚያሳዝን ነው፡፡ ያኔ የነበረው የመነቃቃት ሁኔታ መቀልበሱ ያሳዝናል፡፡ ይህም የመጣው በቅስቀሳው ዙሪያ ገዥው ፓርቲ እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚያደርጉት ቅስቀሳ ሳቢያ የተፈጠረ መፈራቀቅ ነው፡፡ ይህ መጠራጠር በጋራ አገራዊ ቁም ነገሮች ዙሪያ ቁጭ ብሎ ለመመካከር እንቅፋት እንዳይኾንብን ስጋት አለኝ፡፡

ምክንያቱም እንደማየው ምዕራብ ሸዋ ላይ የኾነ ችግር ቢፈጠር እና የሕዝብ ጥያቄ ቢነሣ *‹‹የኦሮሞ ነው››* ነው የሚባለው፤የኢትዮጵያውያን አይደለም የሚባለው፤ አዋሳ አንድ ነገር ቢፈጠር የኢትዮጰያውያን አይደለም የሚባለው፤‹‹የሲዳማ ነው›› ይባላል፡፡ የሕዝብ ጥያቄ እንዲህ ተቆራርሶ እንዲዳከም፣መልስ እንዳያገኝ የሚያደርግ ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ይህን አጥር ካልሰበርን፣ የብሔር ልዩነትን እና የፖለቲካ ድርጅት ድንበርን ተሻግረን መነጋገር ካልቻልን በኢትዮጵያ ለውጥ ለማምጣት፣የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ ለማንቀሳቀስ አስቸጋሪ እንደሚኾን ይታየኛል፡፡

**<u>አዲስ ነገር</u>**፡- በንግግርዎ በሁለተኛው ነጥብ ላይ ሲናገሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የፓርቲዎችን መብዛት እንደ ችግር የሚያዩት ይመስላሉ፡፡

**<u>አቶ ስዬ</u>**፡- የፓርቲዎች መብዛት ተቃውሞን እንደ ማዳከሚያ እና መከፋፈያ ስትራቴጂ ከተወሰደ አደገኛ ነው፡፡ ራሱ ፓርቲው መኖሩ አይደለም ችግሩ፤ ግን የተቃውሞውን ኀይል መበተን፣ ተቃውሞውን መከፋፈል ሆነ፡፡ አርባ እና ኀምሳ የኀጥ ፓርቲ ተደምሮ ውጤት አያመጣም፡፡ ገዥውን ፓርቲ መገዳደር አይቻልም፡፡ ስለሆነም የመከፋፈል ስትራቴጂ ነጸብራቅ ኾኖ ይታየኛል፡፡ የፓርቲዎች መብዛት ዓላማው በርካታ አማራጮች ለሕዝቡ ቀርበውለት ሕዝቡ የተሻለውን ሐሳብ እንዲመርጥ ዕድል ማግኘት መሆኑ ቀርቶ የሕዝቡ ቀልብ እና ድጋፍ በተለያየ መልኩ እንዲበተን ማድረግ ሆኗል፡፡

**<u>አዲስ ነገር</u>**፡- ግን ኢሕአዴግ ብቻ ነው እንዴ እንዲህ እያደረገ ያለው? ለምሳሌ ከመቶ ፓርቲዎች ሃምሳዎቹ የኢሕአዴግ ደጋፊዎች ናቸው እንበል፡፡ ቀሪዎቹ  በሌሎች ግለሰቦችና ቡድኖች የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ተደራጅተው ሲመጡ ደግሞ እውቅና የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**<u>አቶ ስዬ</u>**፡- የሚያሳዝነው ፖለቲከኞች የሚባሉት እና ለኢትዮጵያ ለውጥ እናመጣለን የሚሉትም ለገዥው ፓርቲ ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ የመሆን አዝማሚያ ይታይባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት ይህን ነገር እንደሚደግፈው ጥርጥር የለውም፡፡ ስለሆነም ለምሳሌ በገበያው ስንት ቅንጅት ነው ያለው?

**<u>አዲስ ነገር</u>**፡- በንግግርዎ አራተኛው ነጥብ ላይ ዝምታ በራሱ ሰላም አይደለም፡፡ እንዲያውም በአገራዊ ጉዳይ ላይ ወደ ኀቡዕ፣ወደ ትጥቅ ትግል እያስገባ ነው፡፡ አካሄዱ ደስ አይልም ወይም አማራጩ እርሱ ብቻ ነው ወደሚል ነገር እየተመጣ ነው ብለዋል፡፡ ምን እያሉን ነው?

**<u>አቶ ስዬ</u>**፡- ይህ አሜሪካን አገር በሁሉም ስብሰባዎች ላይ የተጠየቅሁት ጥያቄ ነው፡፡ ኢሕአዴግን በሰላማዊ ትግል ማሸነፍ ይቻላል ወይ? *‹‹ኢሕአዴግ በምርጫ፣ በሰላማዊ መንገድ ሥልጣን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ያለመሆኑ ታይቷል፡፡ ስለሆነም ኢሕአዴግን በሰላማዊ መንገድ በትክክል መቀየር አይቻልም››* የሚሉ ወገኖች ነበሩ፡፡ እኔ ደግሞ የኢሕአዴግ አመራር አባል ነበርኩ፡፡ የትጥቅ ትግል ውስጥ የቆየኹ፣ሠራዊቱን እመራ የነበርኩ ሰው ነኝ፡፡ በዚህ ጉዳይ የእኔን አስተያየት ለማወቅ ጉጉት ነበር፡፡

በምርጫ 97 የነበረው ሁኔታ እና አሁን ያለው ሁኔታ ሲታይ ረጭ ብሏል የሚያሰኝ ነው፡፡ እናም ገዥው ፓርቲ በዚህ ያልኾነ ድምዳሜ ላይ እንዳይደርስ ስጋት አለኝ፡፡ በእኔ

እምነት የሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል አማራጭ ዝግ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል በጥናት ላይ ተመሥርቶ፣ ሥርዐት ባለው መንገድ የተካሄደበት ሁኔታ የለም፡፡ የ97 ምርጫን ሙከራ ብቻ ወስዶ ከእርሱ በመነሣት «ዴሞክራሲያዊ ሥርዐትን በሰላማዊ መንገድ ማምጣት አይቻልም» ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡ ከምርጫ 97 ለቀጣይ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል ብዙ ትምህርቶችን መውሰድ ይቻላል፡፡

በእኔ እምነት የሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል አማራጭ በኢትዮጵያ ተጀምሯል እንጂ አላለቀም፡፡ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግልን ከመንግሥት ለውጥ ባሻገር ነው ማየት ያለብን፡፡ የትጥቅ ትግል መንግሥትን ለመቀየር ያስችል ይሆናል፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዐትን በቦታው ለማስቀመጥ፣የተረጋጋ ማኅበራዊ ኑሮን ለመፍጠር ግን የሚያስችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ገዥው ፓርቲ አሁን ባለው የተቃውሞ ፖለቲካ ሰላም አገኘሁ ብሎ ቢዝናና ተሳስቷል፡፡

<u>አዲስ ነገር</u>፡- የፖለቲካ ችግሮች የጸጥታ ችግሮችን እያስከተሉ ነው የሚል ሐሳብ አንሥተዋል፡፡ በተለይ ደግሞ እርስዎ ለጸጥታ ጉዳዮች የተሻለ ዕውቀት፣የተሻለ ቅርበት ስለነበርዎት እንዲህ ሲናገሩ ክብደት የሚሰጠው ነገር ነው፡፡ እውነት የፖለቲካ ችግሮቹ የጸጥታ ችግር ኾነዋልን? ለዚህስ ማስረጃ አለዎት?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- ለምን አንዳንድ የክስ መዝገቦችን አታዩዋቸውም፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ በየፍርድ ቤቱ የተከፈቱት ፋይሎች ምንድን ነው የሚሉት? «ሕገ መንግሥታዊ ሥርዐቱን ሕገ ወጥ በኾነ መንገድ ለመናድ» ሞክሯል፤ሽብርተኛ ኾኗል፤ ከሽብርተኞች ጋራ ተባብሯል የሚሉ ፋይሎች እና ክሶች ይበዛሉ፡፡ በአገር ውስጥ ያለውን ውዝግብ እንደ አገር ውስጥ ችግር የሚገባውን ትኩረት ሰጥቶ በማለዘብ እና ቁጭ ብሎ በጋራ ተመካክሮ መፍትሔ በማበጀት ፋንታ «ሻዕቢያ የፈጠረው ነው፤እገሌ የፈጠረው ነው» እያሉ ወደ ውጭ መግፋት አግባብ አይደለም፡፡ የውጭ እጅ ጨርሶ የለበትም ማለቴ አይደለም፡፡ ሻዕቢያ በእኛ ውስጥ ችግር በተፈጠረ ቁጥር ከዚያ ትርፍ ለማግኘት እችላለሁ ብሎ የሚጐትተው ገመድ ካለ ጣልቃ ሊገባ ይችላል፡፡ ራሱ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አያያዝስ ለእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ምቹ ሁኔታን እየፈጠረ አይደለም ወይ? የራሳችንን ችግር በመግባባት ብንፈታ የውጭ ኀይሎች ዕድል አያገኙም ነበር፡፡

<u>አዲስ ነገር</u>፡- የፖለቲካ ሥፍራው (political space) በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት የሚያስችል ከኾነ በቁርጠኝነት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የመሥራት ፍላጎት እንዳለዎት

እዚያው አሜሪካን አገር ተናግረዋል፡፡ በምን መለኪያዎች፣ በምን ጥያቄዎች ላይ እና በምን ውክልና (ማንዴት) ነው እነዚህን ኀይሎች ለማቀራረብ እና ለማነጋገር የምችለው ብለው ያስባሉ? የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን እና ፓርቲ መመሥረት እንደማይፈልጉ ተናግረዋል፡፡ ከእርስዎ ጋር ከኢሕአዴግ የተለዩት እነአቶ ገብሩ ዐሥራት የራሳቸው ፓርቲ አላቸው፡፡

<u>**አቶ ስዬ**</u>፡- አብሮ መሥራት ብቻ ነው መንገዱ የሚል ነገር አቅርቤያለሁ፡፡ ይህ ነገር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊያስብበት የሚገባ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ ሁላችንም አስበንበት የሚታየን መንገድ እርሱ ነው ካልን ራሱ ሂደቱ ያገናኘናል፡፡ እኔ በግሌ ማድረግ የምችለውን ለማድረግ ዝግጁ ነኝ፡፡ፓርቲዎች በዚህ መንገድ እንዲሄዱ ከእኔ የሚፈለግ ነገር ካለ የሚቻለኝን አስተዋፅኦ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ፡፡ ለተቃዋሚዎች ብቻ አይደለም፡፡ ኢሕአዴግም በዚህ በጎ መንገድ እንዲሄድ እመኛለሁ፤ከሄደም እደሰታለሁ፡፡ በዚህ መንገድ ለመሄድ የእኔ እገዛ አስፈላጊ ከሆነም ባለኝ አቅም ለመተባበር ዝግጁ ነኝ፡፡ አሁንም አቋሜ ይህ ነው፡፡ ይህን ወደፊት እንዴት ባለ አካኋን ታራምደዋለህ? እንደምን ትገፋበታለህ ለሚለው እያሰብኩበት ነው፡፡ አሁን መናገሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡

<u>**አዲስ ነገር**</u>፡- ከእስር ከተፈቱ ወዲህ እርስዎ ሄደው ወይም እርሱ መጥቶ ያገኘዎት የኢሕአዴግ ከፍተኛ አመራር አባል ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን አለ?

<u>**አቶ ስዬ**</u>፡- አሁን በሥልጣን ላይ ካሉት እኔ ዘንድ መጥቶ ‹‹እንኳን ተፈታህ›› ብሎ የጠየቀኝ ሰው የለም፡፡ ግን በአጋጣሚ ወደ ትግራይ ሄጄ በነበረ ጊዜ መንገድ ላይ ያገኘኋቸው ሰዎች አሉ፡፡ እናም ሰላም ተባብለናል፡፡ ‹‹እንደምነህ፤ ደኅና ነህ ወይ›› ተባብለን፤ተሣስቀን ተለያይተናል፡፡ እዚህ አዲስ አበባ አቶ ዓባይ ፀሐዬ ጎረቤቴ ነው፡፡ እናቱን አውቃቸዋለሁ፡፡ እናቱ አርፈው ኀዘን ተቀምጦ ነበር፡፡ ቤቱ ሄጄ ብርታቱን ይስጥህ ብዬዋለሁ፡፡

ከእነርሱ በኩል ላነጋግርህ ብሎ ወይም እንኳን ተፈታህ ብሎ የመጣ የለም፡፡ ምናልባት አብዛኛዎቹ በመፈታቴ ደስ ሳይላቸው ቀርቶ አይደለም፡፡ ፍርሃት ይኖር ይሆናል፡፡ ከእኔ ጋር መቀራረብ፣ ከእኔ ጋር ሰላምታ መለዋወጥ እንኳን ለእነርሱ ለተራውም ዜጋ አስፈሪ ሁኔታ ይፈጥርም ይሆናል፡፡ አሁን ለምሳሌ ከአሜሪካ እንደተመለስኩ ከጥቂት ቀናት በኋላ በቤቴ አካባቢ ያለው የፖሊሶች እንቅስቃሴ ለውጭ ሰው ያስፈራል፡፡

<u>**አዲስ ነገር**</u>፡- እርስዎስ ሔደው ለማግኘት አልሞከሩም? በተለይ ለአገር ይጠቅማል የሚል ሐሳብ እያቀረቡ ስለሆነ ሔደው ቢያነጋግሩ ምን ነበረበት...

<u>አቶ ስዬ</u>፡- እኔ አልሞከርኩም፡፡ ሐሳቤን ሰምተውታል፡፡ ይህ ለእነርሱም ለመላው ኢትዮጵያም የተወረወረ ሐሳብ ነው፡፡ ስለዚህ ፋይዳ አለው ካሉ ከእኔ ሳይሆን ከራሳቸው መምጣት አለበት፡፡ ከዚያ በላይ መሄዱ ወቅቱ አልመሰለኝም፡፡

<u>አዲስ ነገር</u>፡- *‹‹አቶ ስዬ ቅንጅት ኾነዋል፤ለቅንጅት ይቀሰቅሳሉ››* ብለው ስለሚያወሩት ሰዎች በአሜሪካው ስብሰባ ላይ ሲናገሩ ፡-*‹‹እኔ በኢሕአዴግ ውስጥ ያለኝን ተጽዕኖ ለመሸርሸር የሚያስቡ የፓርቲው ሰዎች ይሆናሉ ይህን የሚያወሩት››* ብለው ተናግረው ነበር፡፡ ቀደም ብለው ደግሞ *‹‹የራሴ ሰው ነኝ፤ፓርቲም የለኝ››* ብለውናል፡፡ ከአሜሪካው ንግግርዎ በመነሣት ግን አሁንም ከኢሕአዴግ የቀረዎት ነገር አለ ብሎ ለማሰብ ይቻላል?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- ቅንጅት መሆን ኀጢያት ነው አልልም፡፡ አሁን የአረና አባል እንዳልሆንኩት ሁሉ የቅንጅት አባልም አይደለሁም፡፡ እኔ ካመንኩበት ቅንጅት መሆን ምንም ወንጀል የለውም፡፡ ነጥቡ ግን ቅንጅት አይደለሁም፡፡ ለምን *‹‹ስዬ ቅንጅት ነው›› ተብሎ እንደሚወራ* አውቃለሁ፡፡ በበርካታ የትግራይ ተወላጅ ዘንድ ቅንጅትን በሚመለከት የተፈጠረ ጥሩ ያልኾነ ግንዛቤ ነው፡፡ በሁሉም ባይኾንም በኢሕአዴግ አባላትም ዘንድ እንደዚሁ፡፡ *‹‹ስዬ የምትሉት ሰዋችሁ ጠላት ከሆነ ድርጅት ውስጥ ገባላችሁ››* ብለው እኔን ከትግራይ ተወላጆች ጋር እንደዚሁም ከኢሕአዴግ ሰዎች ጋር በውሸት ለማራራቅ ነው የሚወራው፡፡ በማንኛውም ድርጅት ውስጥ አባል የመሆን መብት አለኝ፡፡ የድርጅት አባል ስሆን ደግሞ በትኩረት አስቤበት ነው የማደርገው፡፡ ካደረግኹት ግን ስላመንኩበት ነው የማደርገው፡፡ ግን በዚህ ዓይነት መልኩ ከአንድ ድርጅት ጋር የመለጠፍ ችኮላ ጠባብ የሆነ ፖለቲካዊ ምክንያት ነው፡፡

<u>አዲስ ነገር</u>፡- ከኢሕአዴግ ወጥተዋል፡፡ ነገር ግን እዚያ ሳሉ የነበረዎትን መሠረታዊ የአይዲዮሎጂም ይሁን የፖሊሲ ጥያቄዎች በተመለከተ ለውጥ አድርገዋልን? ለምሳሌ የኢሕአዴግ መሠረታዊ አቋሞች ከሚገለጹባቸው ቅራኔዎች መካከል የብሔር ብሔረሰብ ጥያቄ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ የእርስዎ አመለካከት ተለውጧል ወይስ አሁንም እንደዚያው ነው?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- የብሔር ጥያቄ ኢሕአዴግ የፈጠረው ነገር አይደለም፡፡ የኢትዮጵያችን አንድ እውነታ እና ገጽታ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ኅብረ ብሔራዊ አገር ናት፡፡ *‹‹የኢትዮጵያ አንድነት በእኩልነት እና በአክብሮት፣በጋራ መከባበር ላይ መመሥረት አለበት››* የሚለው ቀድሞውንም እኛ ወደ ፖለቲካ ስንገባ ጀምሮ የነበረ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ

አጀንዳ ነው። ስለዚህ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ነባር ጥያቄ ነው ማለት ይቻላል።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- እስር ቤት ብዙ ነገሮችን ለማብሰልሰል ጊዜ ይሰጣል ይባላል። በእስር ቤት ቆይታዎ መሠረታዊ በነበሩ አቋሞች ላይ እንደ ድርጅት ተሳስተን ነበር ወይም በግሌ ተሳስቻለሁ የሚሉት አልያም ልክ ነበርን የሚሏቸውን መሠረታዊ ነገሮች ሊገልጹልን ይችላሉ?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- እኔ እስር ቤት ገብቼ ከብዙ ኢትዮጵያውያን እስረኞች ጋር ተገናኝቻለሁ። ኢሕአዴግን ከውስጥም ከውጭም ኾኜ አይቼዋለሁ። እስር ቤቱ የኢትዮጵያን ገጽታ በአንድ ጠባብ ግቢ ውስጥ ያሳያል። የዳኝነት ነጻነት በምን ሁኔታ ላይ እንደሆነ ያሳያል። የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር በዜጎች ላይ የሚፈጥረውን ግፍ እና ሠቆቃ ታየዋለህ። ስለዚህ ለእኔ ኢሕአዴግን በውስጡ ሆኜ እንዳየሁት ሁሉ ከኢሕአዴግ ውጭ ኾኜ ከዚያም በላይ የኢሕአዴግ ሰለባ ሆኜ ከኢሕአዴግ ሰለባዎች፣ ከኢሕአዴግ ተጠቂዎች ጋር ሆኜ ያየሁበትን ሁኔታ ነው እስር ቤቱ የፈጠረልኝ። ሁለቱንም ገጽታ በደንብ ነው ለመገንዘብ የቻልኹት።

ኢሕአዴግ የታገልኩለት፣ብዙ ችግር ያየሁበት እንደ ግለሰብ ብዙ ዋጋ የከፈልኩበት ሕይወት ነው። ያም ኾኖ ብዙ መሥዋዕት ከተከፈለ በኋላ የኾነውን አይቼዋለሁ። በውጤቱ ደርግን ከመጣል አኳያ የተሳካ ትግል ተካሂዷል። በትንሽ አቅም ግዙፉን ኀይል ለመጣል የሚችል አቅም መገንባት ቀላል ነገር አልነበረም። ብዙ ፖለቲካዊ ኀይሎች አይቻልም ብለው ሞክረው የተዉትን መንገድ ነው እኛ ከዳር ያደረስነው። እናም እንደ ትልቅ ድል ነው የምቆጥረው። ከዚያ አልፎ ግን ዴሞክራሲያዊ ሥርዐትን ከመገንባት አኳያ እንዳልተሳካ አይቻለሁ።

ደርግን ከመጣል ባሻገር የእርስ በርስ ቁጥጥር የሚደረግበት፣ራሱን በራሱ የሚያርም ሥርዐት ገና እንዳልገነባን፣ነጻ ዳኝነት ያለበት የፍትሕ ሥርዐት እንዳላደራጀን፣ ሉዓላዊ ክብሩን ማስጠበቅ የሚችል፣ ሐላፊነቱ እና ተጠያቂነቱ ለኅሊናው እና ለሕገ መንግሥቱ የኾነ ፓርላማ እንዳላቋቋምን እገነዘባለሁ። በኻያ አራት ሰዓት ውስጥ ሕገ መንግሥቱን የሚደረምስ ዐዋጅ ያወጣ ፓርላማ መሆኑ ሲታይ፣ የራሱን ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን የሚገፍ ደንብ የሚያወጣ ፓርላማ ያለን መሆኑ ሲታይ፣በፌዴራላዊ ሥርዐት ስም እጅግ የተማከለ እና በዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት የሚመራ መንግሥት በሥልጣን ላይ መኾኑን ስመለከት በዚህ በኩል ያለብንን ፈተና አለማለፋችን ይታየኛል። ስለዚህም

ያልሞከርናቸው እና በአግባቡ ያልሠራናቸው ወደፊት ልንሠራቸው የሚገቡን ውዝፍ ሥራዎች አሉብን።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- በዚህ በእርስዎ ግምገማ ላይ የሚስማማም የማይስማማ ሊኖር ይችላል። ወደ ዝርዝሩ አንግባ።እስከ አሁን ኢሕአዴግ ውስጥ ቢሆኑና ባይታሰሩ ኖሮ አሁን የሚነገሩን ግምገማ የሚኖርዎት ይመስልዎታል?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- ይህ እንግዲህ እኔ በኢሕአዴግ ውስጥ መቀጠል ስችል እኮ ነው። በዚህ መንገድ መቀጠል አልፈልግም ብዬ ነው የወጣሁት። እንደ ሌሎቹ ልሄድበት ስችል ለኅሊናዬ አይስማማም ብዬ ትቼዋለሁ። ስለዚህ ይህ ግምገማዬ ስለ ታሰርኩ የመጣ ነገር አይደለም። በእርግጥ መታሰሬ ነገሮችን እንደገና በሰከነ መልኩ በስፋት እና በጥልቀት ለማየት ዕድል ሰጥቶኛል።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- ግን እኮ በአደባባይ እንደሰማነው ከሆነ በኢሕአዴግ አመራር መካከል ዋናው ልዩነታችሁ የዴሞክራሲ ጥያቄዎች አልነበሩም። የልዩነት አጀንዳዎቻችሁ ከሉአላዊነት ጋር የተያያዙ ነበሩ።

<u>አቶ ስዬ</u>፡- እንግዲህ በወቅቱ በውይይት መካከል ሳይሆን በጦርነት መካከል ነው የተለያየነው። ጦርነቱ ደግሞ ብዙ ጉዳዮችን አፍረጥርጦ የመጣ ነው። እንደ አገር እንደ መንግሥት ጦርነት ውስጥ ሳንወድ ተገደን ስንገባ ጦርነቱ በርካታ ጉዳዮችን ወደፊት አምጥቷል።ፖለቲካዊ ልዩነቶችን በይፋ ተጠናክረው እንዲወጡ የሚያደርጋቸው በወቅቱ ያለው አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ያ ጦርነት ሲከሠት ደግሞ በዚያ ዙሪያ ልዩነት ተፈጠረ። ግን ጦርነቱ ሁሉን አቀፍ ጉዳይ ነው። ጠባብ መነሻ አይደለም የነበረው።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- የኤርትራ መንግሥት በኾነ መንገድ ቢለወጥ ለውጥ ያመጣል ብለው ያስባሉ?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- እኔ ትልቁ መፍትሔ የምለው ዴሞክራሲን ነው። በሁለቱም አገሮች ዴሞክራሲ እና ነጻነት ሲሰፍን፣ መልካም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት መፈጠር፣ነጻ የሐሳብ ልውውጥ መፈቀድ፣ ለሕዝባቸው፣ለአገራቸው ተጠያቂ የሆኑ መንግሥታት መኖር አለባቸው። ስለዚህ እኔ የመንግሥት መለወጥን ነጻነትን እና ዴሞክራሲን ከማምጣት ፋይዳው ጋር ነው አያይዤ የማየው።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- ለሁለቱ አገሮች ዘላቂ መፍትሔ ስትራቴጂያዊ ኾነው ከተነሡት ጥያቄዎች ዋነኛው የባሕር በር እና የወደብ ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ በምን መልኩ ነው መመለስ ያለበት ይላሉ?

<u>አቶ ስዬ</u>፡- የባሕር በር ጥያቄ ለእኔ የልማት ጥያቄ ነው፤የብሔራዊ ደኅንነት ጥያቄ ነው። የጥያቄውን አንገብጋቢነት ደግሞ በችግራችን ውስጥ አይተነዋል፤እያየነውም ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያ የባሕር በሩን ማግኘት አለባት የሚል እምነት አለኝ። ኢትዮጵያ የባሕር በር ብታገኝ ኤርትራ አትጎዳም። እውነተኛው የኤርትራ ብሔራዊ አገራዊ ጥቅም ሲታይ ኢትዮጵያ የባሕር በር በማግኘቷ የሚነካ አይደለም። ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዳታገኝ ፍላጎት ካለ መንሥኤው፣ምንጩ ኤርትራ አይደለም። ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዳታገኝ የሚፈልጉ ሌሎችም ኀይሎች ነው። ኢትዮጵያ የባሕር በር ያስፈልጋታል ሲባል ደግሞ በመነጣጠቅ መልኩ አይደለም። መለያየታችን የሁለታችንም ደካማ ጐኖች ጎልተው እንዲወጡ አድርጓል። ስለሆነም ኢትዮጵያ የባሕር ባር ያጣችውን ያህል ኤርትራ ከኢትዮጵያ ያጣችው ብዙ ነገር አለ። ይህን ደግሞ ኤርትራ ራሷ በምንም መልኩ ልትሸፍነው የምትችለው ነገር አይደለም። በዕሴቶች መለዋወጥ፣በመልካም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት በመግባባት እነዚህን ነገሮች ሁላችንም በምንጠቀምበት አግባብ መልክ ልናስይዛቸው እንችላለን የሚል እምነት አለኝ።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- ቀደም ሲል መከላከያ ሚኒስትር እያሉ ይናገሩበት የነበረውን የሚያስደነግጥ ድምፀት በመጥቀስ *‹‹አቶ ስዬ አብረዋቸው ላልሆኑ ሰዎች አክብሮት የላቸውም›› ይሉዎታል። ከዚህም በመነሣት ነገሩን ፊት ለፊት እንድለው ከፈቀዱልኝ ‹‹አቶ ስዬ ኩሩ እና ጀብደኛ (proud and arrogant) ናቸው›› እንደሚባሉ ያውቃሉ?*

<u>አቶ ስዬ</u>፡- እኔ አንደኛ ነገር ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት እና በቴሌቪዥን መስኮት ለመታየት ቁጥብ ሰው ነኝ። መከላከያ ሚኒስትርም እያለሁም ይሁን በኋላ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሰጠኋቸው ቃለ መጠይቆች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። በሬዲዮም እንደዚሁ። ለጋዜጣም ሰጥቼ ከሆነ ከመታሰሬ በፊት አንድ ጊዜ ለትግርኛ ጋዜጣ የሰጠኹት ቃለ ምልልስ ነው። ስለዚህ እንደዚያ የሚሉኝ ሰዎች በእውን ያውቁኛል ወይ? እኔ ለማምንበት ነገር እቆማለሁ። ከዚያ ውጭ ግን ይህ ገለጻ ከየት እንደሚመጣ አላውቅም። በእርግጥ ብዙ አልናገርም። ይሄን ኩራት ነው ልትለው ትችላለህ። ምናልባት አንዳንድ ጊዜ የእኔ አማርኛ በተለይ በቀድሞው ጊዜ እንደ ዛሬው የተቀላጠፈ አልነበረም። ከልዩነት በኋላ የቀቡኝ ጥላሸት ሊሆንም ይችላል።

<u>አዲስ ነገር</u>፡- ኢሕአዴግን በተለይም ሕወሓትን ያስታውሱታል፣ አጣሁት የሚል ስሜት አለዎት (ሚስ ያደርጉታል)?

__አቶ ስዬ__ ፡- መቼም የልጅነት ዕድሜዬን ያሳለፍኩበት፣ብዙ መሥዋዕትነትን የከፈልኩበት፣በርካታ ጓደኞቼን ያጣሁበት፣ የትግራይ ሕዝብም በአንድ በኩል ብዙ ችግር እና መከራ በሌላ በኩል ብዙ ጽናት እና አርበኝነት ያሳየበት ትግል ነው። ስለሆነም በድርጅቱ መዋቅር እና ቅርጽ ውስጥ በአካል ባልኖርም ከዚያ የችግር፣የጽናት፣የመተሳሰብ፣የጓደኝነት፣የሕዝብ አክብሮት እና ፍቅር ታሪክ ራሴን ላወጣ አልችልም። ስለሆነም በርካታ በጎ ትዝታዎች አሉኝ።

ያም ኾኖ አሁን ከ33 ዓመት ውጣ ውረድ በኋላ ያ ሁሉ መሥዋዕትነት ተከፍሎ ሲያበቃ ለእነዚያ ሰማዕታት ምንድን ነው የተውንላቸው ሐውልት? ብዬ ተመልሼ ራሴን እጠይቃለሁ። በእርግጥም ልንሠራላቸው ይገባ የነበረው ሐውልት ነጻ ዳኝነት፣የሕግ የበላይነት እንዲኖር እና ለሕገ መንግሥቱ ብቻ ተገዥ የሆነ ሉዓላዊ ፓርላማ እንዲኖር ብናደርግ ነበር ሕያው ሐውልት የሚኾነው። መሸማቀቅ የሌለበት ነጻ የሐሳቦች እና የአማራጮች መንሸራሸር ያለበት ሥርዐት ቢኖር ነበር ቋሚ ሕያው ሐውልት ሠራንላቸው የምለው። ይህን ነገር ግን በተግባር ለማሳካት አልቻልንም። ያላለቀ ሥራ እንዳለብን ነው የሚታየኝ። ስላለፉት ጊዜያት በበጎ የማስታውሳቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉ ሁሉ ያልተሳኩትን ነገሮች ሳይ ደግሞ ሸክሙ ይከብደኛል። እነዚያ በጦርነት ሜዳ የወደቁትን ወንድሞቻችን እና እኅቶቻችንን ስናስብ ማየት ያለብን ያልተቋጨውን እና ከዳር ያልደረሰውን፣እነርሱ የተዉትን ነገር ከፍጻሜ ስለ ማድረስ ነው። ለዚህ ደግሞ ጊዜው የሚጠይቀውን አዲስ ጀግንነት እና የመንፈስ ጥንካሬ መላበስ ይገባል።

__አዲስ ነገር-__ ከእስር በኋላና ከአሜሪካ መልስ ቤተሰባዊ ሕይወትዎ እንዴት ነው?

__አቶ ስዬ__ - እስር ቤት ከነበርነው ሦስት ወንድማማቾች ሁለታችን ተፈተናል። አሁንም ግን አንደኛው ወንድማችን እስር ቤት ነው። ከእርሱ ጋር በአንድ ክስ የተፈረደባቸው ሰው በአመክሮ ተፈተዋል። ይሄ ወንድሜ የእኔ ወንድም በመሆኑ በደርግ ጊዜ አሥር ዓመት ታስሯል። አሁንም የእኔ ወንድም በመሆኑ በእስር ላይ ነው። አሜሪካ ደርሼ ከመጣሁ በኋላ እዚህ ቤቴ የሚገባውን የሚወጣውን እየተከታተሉ ማነህ ከየት ነህ በሚል እየተከታተሉ የመጠየቅ ነገር አለ። ይሄ በሕጻናት ልጆቼ ላይ ስጋት ይፈጥራል። ችግሩ እየተመለሰ ነው ወይ ብለው እንዲጨነቁ ያደርጋቸዋል። የወለዱ ሰዎች ናቸውና ይህን ባያደርጉ ጥሩ ይሆን ነበር። ግን የመጣውን ከመቀበል፣ ከዚሁ ጋር ከመኖር ውጪ ሌላ የሚደረስበት ቦታ የለም።